# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተሃል?

፩. እግዚአብሔር ስለሚያፈቅርህ ለሕወትህ አስደናቂ እቅድ ሰጥቶሃል?

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” ዮሐንስ 3፡16

፪. ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክነያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

“ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።” ሮሜ 3፡23

፫. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

“እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” ዮሐንስ 14፡6

፬. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

“ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።” ዮሐንስ 1፡12

“ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10




“ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ… ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ…” (ማቴ. 22፡ 37፣39)

| | |
|---|---|
| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m. |
| **July 21, 2019** | **ሐምሌ 14፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወንድም ፍቅሩ ካዩ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| ቃል ............. | እህት ሰናይት ከበደ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

“እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።”

(ዘዳ. 6፡ 4-5)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ታብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ፈልጉ

*“ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” (ማቴ. 6:33)*

በዚህ በላይ በሰፈረው ክፍል እግዚአብሔር መለኮታዊውን ቅደም-ተከተል በቃሉ ገልጾልናል። ቅዱሳን ለኑሮ በሚያስፈልግ መብልና መጠጥ፤ ልብስና መጠለያ እንጨነቅ ዘንድ የእግዚአብሔር ሃሳብ አይደለም። የዚህ አለም ሰዎች የሚኖሩበት ቅደም ተከተል በመጀምሪያ ህይወትን ለማሰንበት የሚያስፈልገውን ነገር መፈለግ ነው። ለክርሲቲያን ግን ቅድሚያ መሆን ያለበት ሕይወትን ራሷን የሰጠንን ጌታና አምላክ መፈለግ ነው። ያም ደግም በልጁ የተገለጸውን ጽድቁን እንዲሁም እርሱ የሚገዛበትን መንግስት በመፈለግ ይገለጻል።

መፈለግ የሚጀምረው በልብ ካለ ስፍራ ነው። በልባችን የመጀመሪያውን ስፍራ የሰጠነው ነገር ያንቀሳቅሰናል። መቅደላዊት ማሪያም ጌታ በስሞን ቤት እንዳለ ሰማች። ከዚያም ምንም እንኳ ተጋባዥ ታዳሚ ባትሆንም ያለበት ስፍራ ድረስ ፈልጋ ሄደች። ካገኘችውም በኋላ የከበረ አልብስጥሮስ ሽቶዋን ሰብራ እራሱ ላይ አፈሰሰች። ከዚያም እግሩ ላይ ወደቀችና አመልከችው። መፈለግ እንዲህ ነው። በመኃልይ 1:7 ላይ ሱናማይቱ ሴት “ነፍሴ የወደደችህ አንተ ንገረኝ፤ ወዴት ታሰማራለህ? በቀትርስ ጊዜ ወዴት ትመስጋለህ? ስለ ምንስ ከባልንጀሮችህ መንጎች በኋላ እቅበዘበዛለሁ?” እያለች ውዷን ትፈልገዋለች። ወዴት ነህ ትለዋለች። በእርግጥ ፀሃይ ያጥቁራት እንጂ እስትታገኘው መፈለግዋን አልተወችም።

እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት እግዚአብሔርን በልባችን አንደኛ ማድረግ ነው። እርሱን በልባችን ዙፋን ላይ መሾም ነው። እግዚአብብሔር እስራኤልን እንዲህ ይለዋል፡- “እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ” (ዘዳ. 6፡ 4-5)። የእግዚአብሔር መንግስትና የእግዚአብሔር ጽድቅ (እግዚአብሔር እራሱ) በልባችን የመጀመሪያውን ስፍራ ሲይዝ ነው እግዚአብሔርን የምናመልከው። ያንን ስፍራ ሌላ ማንም ሊይዘው አይገባም። ያንን ስፍራ ሌላ ከያዘው ጣኦት ነው።

መፈለግ ዋጋን ከመስጠት ጋር ይያያዛል። የእግዚአብሔር መንግስት የከበረ መንግስት ነች። በምንም አትለካም፤ ከምንም ጋር አትስተካከልም። በማቴዎስ ፲፡ 44 – 46 ላይ እንደምናነበው የእግዚአብሔር መንግስት “በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፥ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።” እንዲሁም ደግሞ “መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤ ዋጋዋም እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ በአገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት።” በነዚህ ምሳሌዎች የምንረዳው የእግዚአብሔር መንግስት እጅግ የከበረች እንደሆነች እና ለመንግስቱ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀን ወይንም መንግስቱን በምንም ዋጋ ልንለውጠው እንደማንችል ነው።

በመጨረሻም መንግስትቱንና ጽድቁን መፈለግ ማለት መንግስቱና ጽድቁ በህወታችን እንዲሰራና እንድገለጥ መፈለግ ማለት ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔርን መንግስት ስንሻ የምንፈልገው የመንግስቱን ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ ነው። ተጽኖዋን ነው የምንፈልገው። መንግስቱ በተጽኖ የምትገለጥ ነችና እንደ ዘር ታድጋለች፣ እንደ እርሾ ታቦካለች፣ እንደ ብርሃን ታበራለች፣ እንደ ጨው ታሰማለች። ወገኖች አስቀድመን የእግዚአብሔርን መግስት ጽድቁንም እንፈልግ ሌላው ሁሉ ይጨመርልናል። አሜን!